ተግባራዊ የሚሆንበት ቀን፡ ሕዳር 15, 2014

ይህ ማስታወቂያ Inova የእርስዎን የህክምና መረጃ እንዴት እንደሚጠቀምበት፣ እንዴት ለሌሎች እንደሚያጋራው እንዲሁም እርስዎ ይሄንን መረጃ እንዴት ማግኘት እንደሚችሉ የሚመለከት መግለጫ የያዘ ነው።

**እባክዎ በጥንቃቄ ያንብቡት።**

ይህንን ማስታወቅያ በተመለከተ ማንሳት የሚፈልጉት ምንኛውም ጥያቄ ቢኖር፣ በስልክ ቁጥር 571-472-8187 አማካኝነት ወደ ቅሬታ ሰሚ ክፍሉ በመደወል ከዋናው የInova የግል ሚስጢር አያያዝ ሀላፊ ጋራ መገናኘት ይችላሉ።

ወደ ሆስፒታል ሲመጡም ሆነ፣ ሃኪም ወይም ማንኛውም የሕክምና ኣገልግሎት ሰጪ ባለሙያን ሲጎበኙ ጉብኝትዎን የሚመለከት መረጃ ተመዝግቦ ይያዛል። ይህ መዝገብ የህመምዎ ምልክቶች፣ የምርመራና ውጤት፣ ምርመራ፣ ያገኙት የሕክምና ኣገልግሎት፣ የቀጣይ ሕክምና እቅድ እንዲሁም ከክፍያ ጋር የተያያዙ መረጃዎችን ያካትታል። ይህ መረጃ ጥብቅ የጤና መረጃ (PHI) ሆኖ ይያዛል። የጤና መድህን ዋስትና እንቅስቃሴና ሐላፊነት ህግ (HIPAA) በሚጠይቀዉ መሰረት የእርስዎን PHI እንዴት ግልጋሎት ላይ መዋል እንደሚችልና እርስዎ በራስዎ መረጃ ላይ ያለዋቸውን መብቶች በተመለከተ መረጃ እንሰጥዎታለን። ይህ ማስታወቂያ በInova ፋሲሊቲ ወይንም በInova ባለሙያዎች፤ ከInova ጋር በሚሰሩ ተቋማት ወይንም በግል ሃኪምዎ በኩል አገልግሎት ባገኙበት ጊዜ የተመዘገቡ ማህደሮችዎ ላይ ተፈፃሚ ይሆናል። የግል ዶክተርዎ በቢሮም ወይም ክሊኒኩ ውስጥ ተመዝግቦው የሚገኙት የእርሶ መረጃዎች ዶክተሮች እንዴት መጠቀምና ይፋ ማድረግ እንዳለባቸዉ የሚደነግጉ የተለያዩ ፖሊሲዎችና መመሪያዎች ሊያወጣ ይችላል።

**የInova ሐላፊነቶች**

በዚህ የግል ሚስጢር ኣያያዝ ተግባሮችን በተመለከተው ማስታወቂያ ላይ ለሰፈሩ ውሎች ተገዢ የመሆን ግዴታ ኣለብን። በማስታወቂያው ላይ ሰፍረው የሚገኙትን ውሎች በማንኛውም ጊዜ መቀየር እንችላለን። አዲሱ ማስታወቂያ በግዜው እጃችን ላይ በሚገኙት ሁሉም የ PHI መረጃዎች ላይ ተፈጻሚ ይሆናል። በሚያቀርቡት ጥያቄ መሰረት፣ በግል ሚስጢር አያያዝ ማስታወቂያው ላይ የሆነ ማሻሽያ በሚደረግበት ግዜ እናሳውቆታለን። የተሸሻለው ማስታወቂያ ግልባጭ ከፈለጉ በድረ ገፃችን <u>www.inova.org</u> በመጎብኘት፣በስልክ ቁጥር 571-472-8187 በመደወል የተሸሻለው ማስታወቅያ ግልባጭ በበደብዳቤ እንዲላክልዎ በመጠየቅ አልያም በቀጣይ ቀጠሮዎ እንዲዘጋጅልዎ በማሳወቅ ማግኘት ይችላሉ። በዚህ ማስታወቂያ ላይ የተደረጉ መሰረታዊ ለዉጦች ቢኖሩ በቀጣዩ ጊዜ ወደ Inova ፋሲሊቲ ሲመጡ ይህንኑ ለዉጥ የሚገልጽ ግልባጭ እንሰጥወታለን። በተጨማሪ ለውጡ በሚደረግበት ወቅት በድረገጻችን ላይ የሚለጠፍ ይሆናል።

**መረጃዎችን ስለመጠቀም እና ይፋ ስለማድረግ**

**የእርስዎን የህክምና መረጃዎችን እንዴት መጠቀምና ማጋራት እንደምንችል የሚመለከት መረጃ።**

የሚከተሉት ምሳሌዎች የሕክምና መረጃዎችን የምንጠቀምበትና የምናጋራብት ኣሰራር ያብራራሉ፡-

**ለህክምናዊ እንክብካቤ፡-** የህክምና ወይም ሌላ አገልግሎት ለእርስዎ ለመስጠት የሕክምና መረጃዎትን ልንጠቀም እንችላለን። እርስዎን የህክምና መረጃዎች ለዶክተሮች፣ ለነርሶች፣ ለቴክኒሻኖች፣ ለህክምና ተማሪዎች እንዲሁም ለሌሎች በInova ስር ለእርስዎ እንክብካቤ ለሚያደርጉ ሰራተኞች እናጋራለን። ለምሳሌ፣ ቀደም ሲል በInova ተቋም ውስጥ የተደረጉልዎትን የህክምና እርዳታዎችን የሚመለከቱ የህክምና መረጃዎች አሁን ለሚደረግልዎ ሕክምና ኣስፈላጊነት ያላቸው ከሆነ ለInova ሓኪም የምንሰጥ ይሆናል። የተለያዩ የInova ክፍሎች፣ እንደ በሐኪም የታዘዙ መድሃኒቶችን፣ የላብራቶሪ ስራ፣ የምግብና የራጅ አገልግሎቶችን ማስኬድ ይችሉ ዘንድ እረስዎን የሚመለከቱ የሕክምና መረጃዎችን ሊጋሩ ይችላሉ።

ከInova ውጭ ለሆኑ፣ ነገርግን ከእርስዎ ሕክምና ጋር የተያያዙ ኣገልግሎቶችን ለሚያቀርቡ ሰዎችም የእርስዎን የሕክምና መረጃ ልንሰጥ እንችላለን። በተጨማሪም ለሃኪምዎ ወይንም ወደፊት የጤና አገልግሎት ለሚሰጥዎ አካል እርስዎን ለመርዳት በሚያደርገው ጥረት እገዛ ሊያደርጉለት ይችላሉ የምንላቸውን የተለያዩ እርስዎን የሚመለከቱ መረጃዎች ልንሰጠው እንችላለን።

**ክፍያ**፡- ለሚያገኙዋቸው የሕክምና አገልግሎቶች ክፍያ ለመቀበል ሲባል የእረስዎ PHI እንደአስፈላጊነቱ ጥቅም ላይ እንዲውል ይደረጋል። ይህም እኛ የጤና መድህን ዋስትና እቅድዎ ለእረስዎ ልያቀርባቸው የሚገቡ ብለን ያስቀመጥናቸው እንደ - የመድህን ጥቅሞችን የማግኘት ተገቢነት ላይ ውሳኔ መስጠት፣ ለእርስዎ አስፈላጊ ህክምናዎችን ለመስጠት የቀረቡ አገልግሎቶችን ማየት፣ እንዲሁም የዩትላይዜሽን ተግባራትን ከመከለስ ጋር ተያያዥነት ያላቸው ተግባሮችና ማከናወን የመሳሰሉ ኣገልግሎቶች ከማጽደቁ ወይም ክፍያ ከመፈጸሙ በፊት ግምት ውስጥ ሊያስገባቸው የሚችሉ የተወሰኑ ተግባሮችን ያካትታል። ለምሳሌ፤ የሆስፒታል ቆይታዎ ለማጽደቅ ሲባል የእርስዎ ወሳኝ ጥብቅ የሕክምና መረጃ ለጤና እቅዱ ይፋ ማድረግ የግድ አስፈላጊ ሊሆን ይችላል።

**የጤና እንክብካቤ ክንውኖች፡-** የInovaን የቢዝነስ እንቅስቃሴ ለመርዳት የእርስዎን መረጃዎች ልንጠቀምና ልናጋራ እንችላለን። እነዚህ እንቅስቃሴዎች ከብዙ በጥቂቱ የጥራት ግምገማ ተግባሮችን፤ የሰራተኛ ግምገማን፤ የህክምና ተማሪዎችን የማሰልጠን፤ የሙያ ፍቃድ የመስጠት፤ ግብይትና ገቢ ማሰባሰብን እንዲሁም ሌሎች የንግድ ስራዎችን ማከናወን ሊያካትቱ ይችላሉ።

ለምሳሌ፣ በእኛ ተቋሞች ውስጥ የሚገኙትን ታካሚዎች ለማየት ለሚመጡት የህክምና ተማሪዎች የእርስዎን PHI ልንሰጥ እንችላለን። በተጨማሪም በምዝገባ ጠረጴዛ ላይ በተቀመጠው የመመዝገቢያ ወረቀት ላይ የእርስዎን ስም፣ ፊርማና የሃኪሞዎን ስም እንዲገልጹ ልናደርግዎት እንችላለን። እርስዎን ለመርዳት ዝግጁ በሆንንበት ጊዜ በመጠባበቂያ ክፍል ዉስጥ በስምዎ ልንጠራዎ እንችላለን። እርስዎን ለማግኘት ወይም የቀጠሮ ጊዜዎትን ልናስታዉስዎ ስንፈልግ የእርስዎን PHI እንደአስፈላጊነቱ ልንጠቀምም ሆነ ልናጋራ እንችላለን።

ለእርስዎ ኣስፈላጊ ሊሆኑ ስለሚችሉ የሕክምና አማራጮችን ወይም ከጤና ጋር የተያያዙ ጥቅማጥቅሞችን የሚመለከት መረጃ ለእረስዎ ለመስጠት ሲባል እረስዎን PHI እንደአሳፈላጊነቱ ልንጠቀምበት ወይም ልናጋራ እንችላለን። በተጨማሪም ለሌላ የገበያ እንቅስቃሴዎች እርስዎን PHI ልንጠቀም ወይም ልናጋራ እንችላለን። ለምሳሌ፣ ስለምንሰጣቸዉ አገልግሎቶች ወይም እርስዎን ይጠቅማሉ ብለን ያመንባቸዉን የአገልግሎት መረጃዎች ወደ እርስዎ ለማድረስ ስምና አድራሻዎን ልንጠቀም እንችላለን። በ HIPAA የግል ሚስጢር አያያዝ ሕግ መሰረት እነዚህ ተግባሮች እንደማርኬቲንግ አይቆጠሩም።

የእርስዎ PHI ለማርኬቲንግ ተግባሮች የመጠቀም፣ የማጋራት ወይም የመሸጥ እርምጃዎችን መውሰድ ቢያስፈልግ ከእርስዎ በፊርማቸው ካልፈቀዱ በስተቀር አይቻልም።

ሆኖም ግን ከላይ የተመለከቱትን አገልግሎቶች መቀበል የማይፈልጉ ከሆነ በስልክ ቁጥር 571-472-8187 አማካኝነት ወደ ቅሬታ ሰሚ ክፍሉ በመደወል  ዋና የግል ሚስጢር አያያዝ ሀላፊን በማግኘት እነዚህ የማርኬቲንግ ነገሮች እንዳይላኩልኝ ሲሉ ማናገር ይችላሉ።

በቀጣይ ጊዜ ለInova ገቢ ለማሰባሰብ ከምናደርገው እንቅስቃሴ ጋር ተያይዞ እርስዎን ለማግኘት ስንፈልግ የተወሰነ መረጃ ልንጠቀም እንችላለን። በተጨማሪም ይህ መረጃ ለተመሳሳይ ዐላማ ለተቋቋመው ፋውንዴሽናችን ልናጋራ እንችላለን። የሚሰበሰበዉም ገንዘብ ለማህበረሰቡ የምንሰጣቸዉን አገልግሎቶችና ፕሮግራሞች ለማስፋፋትና ለማሻሻል ይዉላል።

ለገቢ ማሰባሰቡ ሂደት ተብሎ ልንጠቀምባቸዉ ከምንችላቸዉ የግል መረጃዎችዎ መካከል የእርስዎ ስም፣ አድራሻ፣ ስልክ ቁጥር፣ አገልግሎት ያገኙባቸው ቀናቶች፣ እድሜ፣ ፆታ፣ እንክብካቤ ያገኙበትን ክፍል የሚመለከት አጠቃላይ መረጃ፣ ህክምና ያደረገልዎት ሃኪም ማንነት እና አጠቃላይ የህክምና ዉጤትዎን ይጨምራል።

ገቢ በማሰባሰቡ ሂደት ወቅት እርስዎን እንድናገኝዎ ካልፈለጉ በ 8095 Innovation Park Drive, Fairfax, VA 22031 የሚገኘውን የInova የጤና ስርአት ፋውንዴሽን ማነጋገር ወይም በስልክ ቁጥር 703-289-2072 መደወል ይችላሉ።

**የቢዝነስ ተባባሪዎች፡-** አንዳንድ በInova የሚሰጡ አገልግሎቶች ከሌሎች የንግድ ተባባሪዎች ጋር በመስማማት ይሰጣሉ። በሶስተኛ ወገኖች አማካኝነት ከምንሰጣቸው አገልግሎቶች መካከል ጽሑፍ የመገልበጥ አገልግሎቶችና  የአገልግሎት ሂሳብ የመሰብሰብ ስራዎች ይገኛሉ። እነዚህ አገልግሎቶች በሶስተኛ ወገን አማካኝነት እንዲሰጡ በምናደርግበት ጊዜ፣ የቢዝነስ ተባባሪዎቻችን የሰጠናቸው ስራዎች በአግባቡ እንዲተገብሩ ይረዳቸው ዘንድ የእርስዎን የጤና መረጃ እንሰጣቸዋለን።  ይህ በምናደርግበት ጊዜ የእረስዎን የጤና መረጃ ሚስጢራዊነት ለመጠበቅ ሲባል የቢዝነስ ተባባሪዎቻችን የእረስዎን መረጃ በአግባቡ እንደሚጠብቁ እናረጋግጣለን።  የእረስዎን መረጃ ሚስጢራዊነት ለመጠበቅ ሲባል መምዋላት የሚገባቸው የInova መለኪያዎች ከእያንዳንዱ አካል በሚደረጉ የቢዝነስ ትብብር ስምምነቶች ውስጥ ተካትተው ይገኛሉ። በተጨማሪ፣ ሁሉም የቢዝነስ ተባባሪዎቻችን በጤናና ሰብአዊ አገልግሎቶች (HHS) ዋና ጸሐፊው አማካኝነት ክትትል የሚደረግባቸው ሲሆን ሁሉም የ HIPAA የግል ሚስጢር አያያዝና ደሕንነት ሕጎችን የሚመለከቱ ድንጋጌዎችን ማክበር ይጠበቅባቸዋል።

**ማውጫ፡-** በፋሲሊቲው ውስጥ ታካሚ ሆነዉ በሚቆዩባቸዉ ጊዚያት ስለ እርስዎ የተወሰኑ መረጃዎችን በፋሲሊቲው ማዉጫ ውስጥ ልናካትት እንችላለን። ይም መረጃ የእርስዎን ስም፣ የፋሲሊቲዉ ዉስጥ አድራሻዎችን እንዲሁም አጠቃላይ ሁኔታዎትን (ለምሳሌ፣መልካም፣ በቂ፣ ወዘተ) እንዲሁም ሀይማኖትዎን ሊያካትት ይችላል። ሃይማኖትዎን የተመለከተ መረጃ ለምእመናን ልንሰጥ የምንችል ሲሆን፣ ሌላ ከሃይማት ውጭ የሆነ የእርስዎን መረጃ ደግሞ የእርስዎን ስም ጠቅሰው ለጠየቁ ሰዎች ልንሰጥ እንችላለን።    በፋሲሊቲው ማውጫ ውስጥ መካተት የማይፈልጉ ከሆነ ማውጫው ላይ ያለመካተት ቅጽ ከመዝገብ ቤቱ ሰራተኞች ወይም ከዋና የግል ሚስጢር አያያዝ ሀላፊው በመጠየቅ ይሙሉ።

**እርስዎን በመንከባከብ ሂደት ላይ ወይም የህክምና ወጭዎችን በመሸፈን የተሳተፉ ግለሰቦች፡-** ለጓደኛዎ ወይም በተደረገልዎት የህክምና እርዳታ የተሳተፉ የቤተሰብ አባላት ወይም የህክምና ወጭዎን ለሸፈኑ ግለሰቦች የእረስዎን መረጃ ልናካፍል እንችላለን። በተጨማሪም የእርስዎ ቤተሰቦች ስለ እርስዎ ወቅታዊ ሁኔታና ያሉበት ቦታ በቂ ግንዛቤ እንዲኖራቸዉ የማድረግ ስራዎችን እያከናወነ ለሚገኝ አካል የእርስዎን መረጃ ልናጋራ እንችላለን። ለጓደኞችዎ ወይም ለቤተሰብዎ አባላት መረጃዎችዎትን የመስጠት ሁኔታን መገደብ ከፈለጉ፣ እነዚህን መረጃዎች የምናጋራው አንድ ግለሰብ መመደብ ይኖርብዎታል።  ይህ በሚሆንበት ጊዜ የወከሉትን ግለሰብ እርስዎን መረጃ ለሌሎች የሚመለከታቸው ወገኖች በምን መልኩ ማጋራት እንዳለበት መመሪያ የመስጠት ሀላፊነት የእርስዎ ይሆናል።

**የምርምር ጥናት፡-** የአንድ ተቋም የግምገማ ቦርድ (IRB)፣ መረጃዎ ጥቅም ላይ እንዲውል ካጸደቀ፣ የእርስዎ መረጃዎች ለምርምር ጥናት የእርስዎን ፈቃድ ሳይጠየቅ ጥቅም ላይ እንዲውል ሊደረግ ይችላል። ምርምር ለማድረግ ዝግጅት ላይ ላሉት ተመራማሪዎችም መረጃዎትን ልንሰጥ እንችላለን። በተጨማሪ፣ ተመራማሪዎቹም እርስዎን በቀጥታ በጥናቱ ዉስጥ ለማሳተፍ ሊያነጋግሩዎት ይችላሉ። ተመራማሪው ስለ ምርምሩ ገለፃ ካደረገልዎት በኋላ ጥያቄ የመጠየቅ እድል ይሰጥዎታል።  በጥናትና ምርምሩ ለመሳተፍ ፍቃደኛ መሆንዎ በፊርማቸው ካረጋገጡ በኋላ በጥናቱ ላይ እንዲሳተፉ ይደረጋሉ።

**የወደፊት ግንኙነቶች፡-** አማራጭ ህክምናዎችን፣ ጤና ነክ መረጃዎችን፣ የበሽታ ቁጥጥር መርሃ ግብሮችን፣  እንዲሁም ፋሲሊቲዎቻች የሚሳተፉባቸዉ የማህበረሰብ ተግባራትን በተመለከተ መረጃዎችን በዜናመጺሄቶች፣ በደብዳቤ ወይም በሌላ አማራጭ ልንልክልዎ እንችላለን።

**የተደራጀ የጤና እንክብካቤ ስርዓት፡-** Inova በሆስፒታሎቹና በሌሎች የተለያዩ ቅንጅቶች አማካኝነት እንክብካቤ የሚሰጥ ሲሆን ይህ ቅንጅታዊ አሰራርም ተጠቃሚዎች ከአንድ በላይ ከሆኑ የጤና እንክብካቤ ሰጭዎች አገልግሎት እንዲያገኙ የሚያስችላቸዉ ነዉ። ይህም አገልግሎት የInovaን ሰራተኞች የሚጨምር ሲሆን ሃኪሞችና በInova ልዩ የክሊኒካል መብት ያላቸዉ በጤና ላይ የሚሰሩ ባለሙያዎችን፣ ተቀማጭነታቸዉ በሆስፒታል የሆኑ እንደ አንስቴዥያ፣ ራዲዎሎጅ፣ ፓቶሎጅ፣ የድንገተኛ ህክምና፣ የክፍሎች ኃላፊዎችና ሜዲካል ዳይሬክተሮችን ያካትታትል። እነዚህ ከላይ የተመለከቱት በሙሉ የInova የጤና እንክብካቤ አደረጃጀት (OHCA) አካል ሲሆኑ ኤሌክትሮኒካዊ የጤና መዝገብ የመረጃ ቋት ሊጋሩ ይችላሉ። ይህ የጋራ ማስታወቂያ የሆነው ሰነድ ለተዘረዘሩት ዐላማዎች ሁሉ እንዲውል ነው እያቀረብንልዎ ያለነው። ሕክምና ለማድረግ፣ ክፍያ ለመፈጸም እዲሁም የጤና እንክብካቤ ስራዎችን ለመስራት እንደአስፈላጊነቱ ይህ መረጃ ጥቅም ላይ ሊውል ይችላል። የቀድሞው ሕክምና PHI በአሁኑ ሕክምና ላይ የራሱ የሆነ ጫና ሊኖረው ስለሚችል፣ ሐኪሞችና ተንከባካቢዎች የቀድሞውን ሕክምና የተመለከተ መረጃ ይዳስሱበት ዘንድ እንዲያገኙት ይደረጋል።

**የጤና መረጃ ልውውጥ፡-** የእርስዎ ጥብቅ የጤና መረጃ በመረጃ ልውውጥ አገልግሎት አማካኝነት ለሌሎች እርስዎን መረጃ የጠየቁ የጤና እንክብካቤ ሰጪዎች በኤሌክትሮኒካዊ መንገድ እንዲያገኙት እናደርጋለን።  በመረጃ ልውውጥ አገልግሎቶች መሳተፋችን እርስዎን የሚመለከቱ የጤና እንክብካቤ መረጃዎች ከሌሎች የጤና እንክብካቤ አገልግሎት አቅራቢዎች እንድናገኝ ይረዳናል።

**እንደ ነጠላ ሆነው የተሸፈኑ አካላት፡-** ለHIPAA ዐላማ ብቻ ሲባል በInova ባለቤትነት ወይም ቁጥጥር ስር ሽፋን የሚያገኙ አካላት በሙሉ እንደ አንድ በተናጠል የተሸፈኑ አካላት ይቆጠራሉ። ሕክምና ለመስጠት፣ ክፍያ ለመፈጸምና የጤና እንክብካቤ ስራዎችን ለማከናወን ሲባል እንደአስፈላጊነቱ PHI በተናጠል ለተሸፈነው አካል ጨምሮ በሌሎች ፋሲሊቲዎች ለሚሰሩ ሰዎች የሚሰጥ ይሆናል። ሌሎች ፋሲሊቲዎች ላይ የሚሰሩ የጤና እንክብካቤ ባለሙያዎች አሁን ለሚሰጡት ሕክምና ሲባል የቀድሞው የሕክምና መረጃዎችን መዳሰስ ሊኖርባቸው ስለሚችል PHI ባሉበት ቦታ እንዲያገኙ ሊደረግ ይችላል።  በዚህ ሽፋን በሚሰጠው ቅርንጫፍ ድርጅት ውስጥ ስላሉ ሌሎች ቦታዎች ተጨማሪ መረጃ ለማግኘት እባክዎ የግል ሚስጢር አያያዝ ዋና ሀላፊን ያናግሩት።

**በህግ በተደነገገዉ መሰረት፣** የጤና መረጃ ቀጥለው ከተዘረዘሩት ወገኖች ጋር መጋራት እንችላለን፡-

- የምግብና መድሃኒት አስተዳደር
- በሽታን፣ ጉዳትንና አካለዊ ጉዳትን የመከላከልና የመቆጣጠር ሃላፊነት የተጣለባቸዉ የህዝብ ጤና ጥበቃ ወይም ሕጋዊ ባለስልጣናት
- የማረሚያ ተቋማት
- የሰራተኞች ካሳ ወኪሎች
- የሰዉነት ክፍልና ጅማት ለጋሽ ድርጅቶች
- የጦር ሐይል መመሪያ ባለስልጣኖች
- የጤና ቁጥጥር ወኪሎች
- የቀብር አስፈፃሚዎች፣ የሟችን አሟሟት የሚያጠኑ ሰዎችና የሜዲካል ዳይሬክተሮች
- የብሄራዊ ደህንነትና የኢንተሊጀንስ ኤጀንሲዎች
- ለፕረዚደንቱና ለሌሎች ባለስልጣናት የጥበቃ አገልግሎት ሰጭዎች

**የህግ መስከበር/ሕጋዊ ስነስርዓቶች፡-** ሕክ ለማስከበር ስራዎች ሲባል የጤና መረጃ ልናጋራ እንችላለን፡-

- በፍርድ ቤት ትዕዛዝ፣ ሕጋዊ የጥሪ ጥያቄ፣ የፍርድ ቤት መጥሪያ ወይንም ተመሳሳይ ሂደቶች፤
- በወንጀል ድርጊት ምክንያት ተከስቷል ብለን የምናምነው ሞትን አስመልክቶ፤
- በInova ተቋም ውስጥ ስለተፈፀሙ የወንጀል ድርጊቶች፤
- በተለያዩ መሳሪያዎች የደረሱ የመቁሰል አደጋዎች

**ክፍለግዛቶችን ብቻ የሚመለከቱ መስፈርቶች፡-** የጤና ማሻሻያዎች ወይም የጤና እንክብካቤ ወጭዎች ቅነሳ ዙሪያ ህዝብን መሰረት ያደረጉ እንቅስቃሴዎች በብዙ ክፍለ ግዛቶች አስቀድሞ የማሳወቅ መስፈርት ተግባራዊ ሁኖባቸዋል። አንዳንድ ክፍለግዛቶች ተጨማሪ የሕግ መስፈርቶችን የሚሹ የግል ሚስጢር አጠባበቅ ሕጎችን በተናጠል አውጥተዋል። የቨርጂኒያ ህግ ከፌደራሉ ህግ በተሻለ ሁኔታ ጥበቃ የሚያደርግ ሆኖ ከተገኘ ተፈፃሚነት ይኖረዋል።

እርስዎን PHI በማስታወቂያው ከተገለጸው ውጭ ለሌላ ጉዳይ መጠቀም ወይም ማጋራት ቢያስፈልግ፣ እራስዎ ወይም በተወካይዎ በኩል በሚሰጡት የጽሑፍ ፍቃድ ብቻ ተመስርቶ የሚከናወን ይሆናል። በጽሑፍ የተሰጡ ፍቃዶችን መረጃውን እንዲጠቀም ወይም እንዲያጋራ ፍቃዱ ወደ ተሰጠው ክፍል በማሳወቅ ሊሰረዙ ይችላሉ።

**የእርስዎ የመረጃ መብቶች፦**

ምንም እንኳን የጤና መረጃ ባለቤትነቱ የጤና እንክብካቤ ባለሙያው ቢሆንም እርስዎም በመረጃዎቹ ላይ **የሚከተሉት መብቶች** ይኖርዋቸዋል፦

- ***መመርመርና ግልባጭ መያዝ፦*** በእኛ ይዞታ ስር ያሉና ስለህክምናዎ ውሳኔ ለመስጠት ጥቅም ላይ ሊውሉ የሚችሉ ሕክምናዊ መረጃዎችን መመርመርና ግልባጫቸውን መውሰድ ይችላሉ። ይህም መብት የህክምናና የክፍያ መዝገቦችን የሚጨምር ሲሆን የሳይኮቴራፒ መዝገቦችን አያካትትም። በInova ኢሌክትሮኒካዊ የጤና መዝገብ (EHR) የሚገኙትን የእረስዎ የ PHI መረጃዎችን ኤልክትሮኒካዊ ግልባጭ እንዲሰጥዎ መጠየቅ ይችላሉ። ጥያቄ ዎ ተቀባይነት ካገኘበት ቀን አንስቶ ባሉት 15 ቀናት ውስጥ መረጃዎትን የማግኘት እድል ሊሰጥዎ ይገባል። ነገር ግን በጣም በተወሰኑ ሁኔታዎች ላይ በመዝገብዎ ላይ የሰፈሩትን መረጃዎች ለመመርመርና ግልባጭ ለመውሰድ ያቀሩቡት ጥያቄ ውድቅ ልናደርግብዎት እንችላለን። ሕክምናዊ መረጃ እንዳያገኙ ከተደረገ፣ ውሳኔው እንደገና እንዲታይልዎ ሊጠይቁ ይችላሉ። ቀድሞ በተደረገው ክልከላ ላይ ያልተሳተፈ የሙያ ፈቃድ ያለው የጤና ባለሙያ በInova ተመርጦ እንደገና ያቀረቡት ጥያቄንና የክልከላ ውሳኔውን እንዲያጤን ይደረጋል። ለሚወሰነው ውሳኔ ተገዢ እንሆናለን።

- ***በመዝገብዎ ላይ የሰፈሩትን መረጃዎች ለማሻሻል ስለመጠየቅ፦*** በእኛ የተያዙ የህክምና መረጃዎት ትክክል እና ሙሉ አይደሉም ብለው የሚያምኑ ከሆኑ ይህንኑ ለማስተካከል ጥያቄ ማቅረብ ይችላሉ። መረጃዎ በInova ይዞታ ስር እስካለ ድረስ መረጃዎትን ለማስተካከል ጥያቄ የማቅረብ መብት አለዎት። ነገር ግን በአንዳንድ ሁኔታዎች ላይ ተመስርተን ይህንን መረጃ የማስተካከል ጥያቄዎትን ዉድቅ ልናደርግ እንችላለን። ይህም ከሆነ ጥያቄዎ ተቀባይነት ያላገኘበትን ምክንያት የምንገልጽልዎ ሲሆን HIPAA የግል ሚስጢር አጠባበቅ ሕግ ላይ በተደነገገው መሰረት አማራጭ መፍትሔ የሚቀርብልዎ ይሆናል።

- ***ይፋ የተደረጉ መረጃዎችን ስለመጠየቅ፦*** ከህክምና፣ ከክፍያ ወይም ከጤና እንክብካቤ ኦፕሬሽኖች ዉጭ መረጃዎት ለሌሎች ጉዳዮች ጥቅም ላይ አለመዋላቸዉን ለማረጋገጥ ሪፖርት የመጠየቅ መብት አለዎት።

- ***ለተወሰኑ አገልግሎቶች መረጃ እንዳይሰጥ የማገድ መብት***

    - *ሙሉ ወጪዎን ከኪስዎ በመሸፈን ያገኙዋቸውን አገልግሎቶች የሚመለከቱ የጤና መረጃዎች ለሌላ አካል እንዳይጋሩ የማገድ ጥያቄ ማቅረብ ይችላሉ። ይህ ጥያቄ መቅረብ ያለበት አግልግሎቱ ከመሰጠቱ በፊት ሲሆን፣ መረጃው የሚጋራው ለጤና እቅድ ዐላማዎች ክፍያ ወይም የጤና እንክብካቤ ስራዎች ከሆነ ብቻ ነው።*

    - ከሕክምና፣ ክፍያ ወይም የጤና እንክብካቤ ስራዎች ጋር በተያያዘ የምንጠቀምበትን ወይም የምናጋራውን የእረስዎን የሕክምና መረጃ ለማገድ ወይም ለመቀነስ ጥያቄ ማቅረብ ይችላሉ። በተጨማሪ እንደ የቤተሰብዎ አባል ወይም ጓደኛ የመሳሰሉ፣ በእርስዎ እንክብካቤ ላይ ለሚሳተፉ ወይም ለእንክብካቤዎ ለሚከፍሉ ሰዎች፣ ያለውን የሕክምና መረጃ ማጋራቱን የመገደብ ጥያቄ የማቅረብ መብት ኣለዎት። ለምሳሌ፣ የቀዶጥገና መረጃዎትን እንዳናጋራ ሊጠይቁን ይችላሉ።

      እገዳው **የሚስጢራዊ ግንኙነት ጥያቄና/ወይም የማጋራት እገዳ የሚሉ ቅጾችን በሞሙላት በጽሑፍ ማቅረብ ይቻላል።** የዚህን ቅጽ ቅጂ አገልግሎት ለማግኘት በሚመዘገቡበት ወቅት መውሰድ ይችላሉ፣ አልያም ከድረገጻችን www.inova.org ማግኘት ይችላሉ።

    - **ከኪስዎት በከፈሉት ገንዘብ ካገኙዋቸው አገልግሎቶችና አሰራሮች ውጭ በሆኑ መረጃዎች ላይ እገዳ እንድናደርግ ቢጠይቁን፣ ጥያቄዎን የመቀበል ግዴታ አይኖርብንም።** ከሕክምና፣ ክፍያዎችን እና የጤና እንክብካቤ ስራዎችን በተያያዘ የምንጠቀምባቸው ወይም የምናጋራቸው የእርስዎ መረጃዎች ላይ እገዳ መጣልን አስመልክቶ የሚያቀርቡት ጥያቄ ለግል ሚስጢር አጠባበቅ ዋና ሀላፊው መሰጠት ይኖርበታል። እነዚህን የእገዳ ወይም የመገደብ ጥያቄዎችን ሊያጽድቅ የሚችለው የግል ሚስጢር አጠባበቅ ዋና ሀላፊው ወይም ተወካዩ ብቻ ይሆናል። ጥያቄዎ ከተቀበልነው፣ መረጃዎ ለእረስዎ የአስቸኳይ ጊዜ ሕክምና ለመስጠት ካልተፈለገ በስተቀር ጥያቄዎትን አክብረን እንቀጥላለን።

- ***ግንኙነቶች ሚስጥራዊ እንዲሆኑ ስለመጠየቅ፦*** ከእኛ ጋር የሚያደርጓቸዉ ግንኙነቶች በሙሉ ሚስጥራዊ እንዲሆኑና በተወሰኑ ቦታዎች እንዲሆኑ የመጠየቅ መብት አለዎት። ለምሳሌ፤ እኛ እርስዎን ለማግኘት ስንፈልግ የመገኛ ቦታዎትን ከመኖሪያ አድራሻዎ ዉጭ ወይም በ ዩ.ኤስ አሜሪካ ደብዳቤ እንዲሆን ሊጠይቁን ይችላሉ። ይህ አይነቱ ጥያቄ በጽሁፍ መቅረብ ያለበት ሲሆን የአገልግሎት ክፍያዎችና ሌሎች የአገልግሎት መቀበያ የፖስታ አድራሻን ማካተት አለበት። በዚህ ኣጋጣሚ ሊሰመርበት የሚገባዉ ጉዳይ መልዕክት ተልኮልዎት ምላሽ የማይሰጡ ከሆነ Inova እርስዎ ከመረጡት ሁኔታና ቦታ ዉጭ ሌላ እርስዎን የሚያገኝበት ዘዴ ሊጠቀም እንደሚችል ነው። እርስዎ ከመረጡት ዘዴና ቦታ ውጭ ልናገኝዎት ከመሞከራችን በፊት እናሳውቅዎታለን።

- ***ጥሰትን ስለማሳወቅ፦*** የእርስዎን (PHI) በሚጣስበት ጊዜ ይህንኑ የማወቅ መብት አለዎት።

- ***የዚህን ማስታወቅያ የወረቀት ግልባጭ፦*** የዚህን ማስታወቂያ ቅጂ የማግኘት መብት አለዎት። ይሄንን ማስታወቂያ በኤሌክትሮኒካዊ መንገድ ለመቀበል የተስማሙ እንኳ ቢሆኑ፣ የዚህን ማስታወቂያ ቅጂ በየትኛውም ጊዜ እንሰጦት ዘንድ መጠየቅ ይችላሉ።

የዚህ ማስታወቅያ ቅጂ ከድረገጻችን http://www.inova.org ላይ ማግኘት ይችላሉ።

ከዚህ ማስታወቅያ ጋር የተያያዙ መብቶችዎን ለመጠቀም፣ እባክዎ አገልግሎቶች ካገኙበትና ትያቄዎን በጽሑፍ ካስገቡበት የፋሲሊቲው የምዝገባ ክፍል ጋር በመሄድ ለዚህ ጉዳይ የሚያስፈልጉ ቅጾችን ይውሰዱ። ከፈለጉ ደግሞ እነዚህን ቅጾች ከድረገጻችን http://www.inova.org ላይ ማግኘት ይችላሉ።

በዚህ ማስታወቅያ ላይ ለውጥ ስለማድረግ

ይህ ማስታወቂያ በፈለግነው ጊዜ የመለወጥ መብት አለን። የተለወጠዉ ማስታወቂያ በእኛ ይዞታ ባሉ የእርስዎ መረጃዎች ላይና በቀጣይ በምንቀበላቸው መረጃዎች ላይ ተፈጻሚ ይሆናል። ያሁኑ ወቅታዊ ማስታወቅያ ተግባር ላይ የሚዉልበትን ቀን አካቶ በInova ፋሲሊቲዎች ይለጠፋል። በተጨማሪ፣ ወደ Inova እንደ ውስጥ ታካሚ ወይም ተመላላሽ ታካሚ ሆነው የሕክምና ወይም የጤና እንክብካቤ አገልግሎት ለማግኘት በሚመጡበት እያንዳንዱ ጊዜ በወቅቱ ያለውን አዲስ ማስታወቅያ እንዲያገኙ እናደርግዎታለን። ከድህረ ገፃችን http://www.inova.org ላይ ወቅታዊ የሆነውን መረጃ በፈለጉት ጊዜ ማግኘት ይችላሉ እንዲሁም ወቅታዊ የሆነው እትም በፖስታ ይላክልዎ ዘንድ በስልክ ቁጥር 571-472-8187 በመደወል ጥያቄ ማቅረብ ይችላሉ።

ቅሬታዎች

የግላዊነት መብትዎ ተጥሷል ብለው ካመኑ፣ ቅሬታዎን ወደ 8095 Innovation Park Drive, Fairfax, VA 22031፣ የሚገኘዉ የInova የቅሬታ ሰሚ ክፍል ማቅረብ ይችላሉ። የግል ሚስጢር አጠባበቅ ዋና ሀላፊ። ቅሬታዎን ወደ ጤናና ሰብአዊ አገልግሎቶች ክፍል ዋና ጸሐፊ ማቅረብ ይችላሉ። ወደ ዋና ጸሐፊው ቅሬታ ማስገባትን የሚመለከቱ መመሪያዎች www.hhs.gov/ocr/privacy ላይ ይገኛሉ።

ሁሉም ቅሬታወዎች በጽሑፍ መቅረብ ይኖርባቸዋል። **የInova የግል ሚስጢር አጠባበቅ ተግባሮችን በተመለከተ ቅሬታ በማቅረብዎ ምክንያት የሚጠብቅዎት ቅጣት የለም።**

ሌሎች የሕክምና መረጃ ጥቅሞች

ለእርስዎ ያቀረብንልዎትን ሕክምና የሚመለከቱ መረጃዎች መዝግበን ማስቀረት ይጠበቅብናል። Inova የእርስዎን መረጃ በዚህ ማስታወቅያ ላይ ላልተካተቱ ሌላ ምክንያቶች ወይም እኛን ከሚመለከቱ ሕጎች ውጭ ጋር በተያያዘ ለመጠቀም ወይም ለማጋራት የእርስዎ የጽሁፍ ፈቃድ ማግኘት የግድ ይሆናል። የሕክምና መረጃዎን እንድንጠቀምበት ወይም እንድናጋራው የሰጡንን ፈቃድ፣ በፈለጉት ጊዜ በጽሑፍ በማሳወቅ መሰረዝ ይችላሉ። የሰጡንን ፈቃድ እንድነሰርዝ የሚገልጽ ጽሑፍ ከተቀበልን፣ የእርስዎን የሕክምና መረጃ መጠቀምም ሆነ ማጋራት የምናቆም ይሆናል። በፈቀዱልን ጊዜ ያጋራነው መረጃን ግን መልሰን መውሰድ አንችልም።

**የግል ሚስጢር አጠባበቅ ዋና ሀላፊ**

ስልክ ቁጥር፦ 571-472-8187